ጥቅምት 12 ቀን 2001 ዓ.ም

# አቶ ሌንጮ ለታ ምንድን ነው የሚሉት?

ከ አያልነሽ

ሰሞኑን አቶ ሌንጮ ለታ ጠፍተው ከከረሙበት የፖለቲካ መድረክ በእግር በፈረስ ተፈልገው ከህዝብ ጋር ሊያገናኙአቸው በጣሩ ሰዎች አማካኝነት፣ የአቶ ሌንጮን ድምፅ ሰምተናል። በእንግድነት የተጋበዙበት ወቅትና ጊዜም ራሱ አነጋጋሪና ጆሮን የሚስብ ሆኗል። ይሁን እንጅ አቶ ሌንጮ ይህንን አጋጣሚ ተጠቅመው ቀደም ሲል ይመሩት ስለነበረው ድርጅታቸው ኦነግና፣ ዛሬ እሳቸው ስለሚገኙበት ሁኔታም በስፋት ማብራሪያ ሰጥተዋል። በቅድሚያ አቶ ሌንጮ አጥብቀው ያሳሰቡት ጉዳይ ቢኖር በዚህ በተጋበዙበት መድረክ፣ ድርጅታቸው ስለነበረው ኦነግ አሁን ሊናገሩ እንዳማይፈልጉና በዚህ ዙሪያም ጥያቄዎች እንዳይጠየቁ፣ ከተነሳም ለመመለስ ፈቃደኛ እንዳልሆኑ አሳስበዋል። በዚህ መድረክ ሲቀርቡም በግላቸውና የግላቸውን ሃሳብ ሊያስረዱ እንደመጡ አበክረው ገልጠዋል። እኔም የአቶ ሌንጮን ማሳሰቢያ ግምት ውስጥ በማስገባት በተቻለኝ መጠን በእንግድነት በተጋበዙበት መድረክ ቀይታቸው ላይ አተኩሬ በጉዳይ ላይ ሃሳብ ቢኖረኝ፣ የግሌን ለመጻፍ ፈቀድሁ።

የተከበራችሁ አንባቢዎቼ ሆይ! ዛሬ ልጽፈበት የተነሳሁበት ጉዳይ በአቶ ሌንጮ ቆይታ ላይ ያተኮረ ይሁን እንጅ፣ አቶ ሌንጮ ያቀረቡትን ሃሳብ ለማየትና ለመዳሰስ ስሞክር፣ አቶ ሌንጮን ከኦነግ ለይቶ ለማቀረብ ምን ያህል እንደሚችግርና እንደሚከብድ ተረዱታላችሁ። (አቶ ሌንጮም ይረዱልኛል ብዬ ስለምገምት) የሰጋሁበት አጋጣሚ ቢፈጠር ምክንያቱን እንድትረዱልኝ ከታላቅ አክብሮት ጋር በትሕትና እጠይቃለሁ። እንዲህም ሆኖ ግን በተቻለኝ መጠን አሁንም ላተኩርበት የምሻው አቶ ሌንጮ ባቀረቡት ሃሳብ ዙሪያ ላይ ለማድረግ ነው የምጥረው። ለማንኛውም እስቲ አቶ ሌንጮ በመድረኩ ሲቀርቡ ያቀረቡትን ማሳሰቢያ ከአንደበታቸው ልጥቀስ፦

> « በቅድሚያ እንደምን ዋላችሁ። ስለጋበዛችሁኝ በጣም አመሠግናለሁ። ቀደም ብዬ ለማስታውቅ የምፈልገው እኔ በኦነግ ስም ለመናገር በአሁኑ ጊዜ ሥልጣን የለኝም፤ መብትም የለኝም። ስለዚህ ድርጅቱን፣ የድርጅቱን ሁኔታና የአሁኑን ፖሊሲ በተመለከተ ጥያቄ ባታቀርቡልኝ እወዳለሁ። ላለፉት ሁኔታዎች ወይም የእኔ የግል አስተሳሰቤን ለማወቅ ስትፈልጉና ብትጠይቁኝ

EthioLion.com

መልስ እሰጣለሁ፤ በኦነግ ፈንታ ግን ለመናገር አልችልም ይሄ እንዲታውቅልኝ እፈልጋለሁ።»

እኔም እንግዲህ ይህንን ማሳሰቢያ ግምት ውስት በማስገባት ነው አቶ ሌንጮ ባቀረቡት ጭብጥ ላይ ማተኮሩን የመረጥኩትና የምመርጠው። በነገራችን ላይ ምናልባት አልፎ አልፎ ከአቶ ሌንጮ ጋር በተያያዘ ኦነግ አብሮ ቢነሳና ላነሳው ብሞክር፤ ኦነግና አቶ ሌንጮ በረዥሙ ጉዞ ውስጥ አብረው ተያይዘው የቆዩ በመሆናቸው እንደሆነ ግምት ውስጥ እንድታስገቡት አሁንም በድጋሚ አጥብቄ እጠይቃለሁ።
መልካም! ወደተነሳሁበት ጉዳይ ልግባ። ለመሆኑ አቶ ሌንጮ ምንድን ነው የሚሉት? እጠቅሳለሁ፥

በፖለቲካ ትግል በምን ዓይነት ሁኔታ ነው ገብተህ የተሠማራኸው ለተባለው ጥያቄ የ60 ዎቹ ዘመናት ወጣት በሙሉ ተማሪ የነበረ በተማሪ እንቅስቃሴ በስፋት ባይሳተፍም፣ የፖለቲካ ለውጦች እንዲሆኑ፣ እንዲከሰቱ የማሰብ . . . . ተቋረጠ፤ እንደገና ከአቋረጡበት ቀጥለው ኢትዮጵያን አቀፍ የሆኑ ድርጅቶች ነበሩ ኢዲዩ ያኔ። ኢዲዩ በምንም ዓይነት ሊስበኝ የሚችል ድርጅት አልነበረም፤ ኢሕአፓና መኢሶን ደግሞ ምን ላይ እንደተጣሉ፣ ልዩነታቸው ምን ላይ እንደሆነ መረዳት አልቻልኩም። ለምሳሌ ”ያቸንፋልና ያሸንፋል" መካከል ያለው ልዩነት ለእኔ ምንም ፍች አልነበረውም፤ ”ላብ አደርና ወዛደር” ተብሎ መገዳደል ፍቹም አልገባኝም። ስለዚህ እኔ ወደዚያ አልተሳብኩም። ከፍተኛው ነገር፣ እኔ የተሰማኝ የብሔሬ ጭንቀት፣ የብሔሬ መዘረፍ፣ የኦሮሞ ብሄር መጨቆን ይሄ ነበር የተሰማኝ። ለዚያ ደግሞ ማንኛውም ሰው መጀመሪያም ከቤቱ ነው የሚነሳው። ለእኔ ደግሞ የኦሮሞ የህዝብ ጥያቄ ነው ከሁሉም አስቀድሞ የሚታየኝ ዛሬም ቢሆን... ይላሉ!

እጅግ አስገራሚና አስደናቂ ነገር! ታሪክ ነው። ለመሆኑ ያኔ በ60ዎቹና ከ60ዎች ቀደም ብለው የነበሩት የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታዎች አቶ ሌንጮ ለታ እቆሙበት ላይ ቆመው እንደተናገሩት፣ ከላይ እንዳሉትና እንዳስቀመጡት ነበርን? እውነት ያ ትውልድ (እሳቸውም ጭምር) የታገለውና የሞተው ለ ”ቸ" እና ለ "ሸ" ”ላብ አደርና ወዝአደር" ለሚባሉት ቁንጽል ቃላት ነበር? እውነት ያኔ እነኝህ ነበሩ የሚባሉ ድርጅቶች ከመፈጠራቸው በፊትስ ኢትዮጵያ ውስጥ ጭቆናና ትግል አልነበርም ነው የሚሉት? የጎጃም ገበሬዎች አመጽ፣ የሜጫ ቱለማ እንቅስቃሴ፣ የ53-ቱ የእነ መንግስቱ ነዋይ መፈንቅለ ሙከራ፣ በመላ ኢትዮጵያ የገበሬዎች አመጽ፣ በተለይም በደቡብ ኢትዮጵያ የነበረው ገበሬ፣ የመሬቱ ባለቤትነት ተነፍጎት በጭሰኝነትና ሕይወቱ በአሳዳሪው እጅ በወደቀበት ሁኔታ፣ ያኔ እውነት ጭቆናው አቶ ሌንጮ ለታ

እንዳቀረቡት የአንድ"ብሔር" ጭቆና የአንድ "ብሔር" ጉዳይ ብቻ ነበርን? ኢትዮጵያ ውስጥ የሴቶች ጭቆና አልነበረም ይላሉ ? የወታደሮች አመጽ አልነበረም? አቶ ዘውዴ ረታ አርዕስት አድርገው 572 ገጽ የጻፉበት ”የኤርትራ ጉዳይስ"? አቶ ሓዲስ አለማየሁ የጻፉት አስደናቂውና የማይሰለቸው "ፍቅር እስከ መቃብር" መጽሐፍ... የተጻፉት ከኢትዮጵያ ምድር ጋር ያልተገናኙና ያልነበሩ የማይዛመዱ ታሪኮች ናቸው? ምንድር ነው የሚሉት አቶ ለንጮ? ዛሬስ አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ተጨባጭ ሁኔታ በተለይም ከግንቦቱ 1997 ምርጫ በኋላ፣ አቶ ሌንጮ ኢትዮጵያን የሠራት ”የአማራው ነፍጠኛ ገዥ መደብ" ነው ብለው ነው የሚያምኑት? ግንቦት 1997 ዓ.ም አንግቧቸው የተነሳው ጥያቄዎች ምን ነበሩ? የግንቦት 7/1997 የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥያቄዎችና ፣ እርስዎ የተሳተፉበት የያኔው የየካቲት 1966 አብዮት ጥያቄዎችና መፈክሮች ምን ምን ነበሩ? በአሁኑ የግንቦት 1997 እና በያኔው የየካቲቱ 1966 አመጽን የወለዱ ጥያቄዎች ዛሬ እርስዎ እንደሚሉትና እንደሚያስጨንቅዎት በአንድ የጠበበ ጥያቄና ጉዳይ ብቻ ላይ ያተኮረ ነበርን? ከየካቲት 66ቱ ህዝባዊ ጥያቄና አመጽ ካልተማርን፣ ከ40 ዓመት በኋላ ከግንቦቱ 1997 ምርጫስ ልንማረው የሚገባንና የኢትዮጵያ ሕዝብ ያስተላለፈልን መልዕክትስ ምንድን ነው? ወዘተ . . .

በአጭሩ በእነኝህ ከላይ በዘረዘርኳቸው ጉዳዮች ላይ አንዳንድ ነገሮችን ለማንሳት ተገደድኩ። እባክዎ! አቶ ሌንጮ በጥሞና እንዲከታተሉኝና በጉዳዩ ላይ ክብደት ሰጥተው ውይይት ብናደርግ ወደ መፍትሄ ያደርሳናል ብዬ ጽኑ ዕምነት አለኝ ። እኔ አሁን መነሻዬና መንደርደሪያዬ ላደርገው ያቀድኩት የሩቁን የያኔውን የየካቲቱ የትግል ጉዞ ሳይሆን፣ የአሁኑን የቅርብ  የግንቦት 1997 ተጋድሎዎችና ያነሳቸው ጥያቄዎች አንድምታና፣ ከገዥው ቡድን የተሰጠቸው መልሶች መሠረታዊና ለእኔና ለእርስዎ የመከራከሪያ ሃሳብ ሊሆን ይችላል ብዬ እገምታለሁ። የግንቦት 1997 ምርጫ የጠየቃቸው ጥያቄዎች የጠበቡ ሳይሆኑ እጅግ ሰፊ ይዘት ያላቸው ነበሩ። ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፦

- የዴሞክራሲ ጥያቄ - ማለትም የማንበብ፣ የመጻፍ፣ የመደራጀት፣ ሃሳብን ያለ ተፅእኖ የመግለጽ፣ ከቦታ ቦታ የመንቀሳቀስ ወዘተ...
- የሥልጣን ባለቤትነት ጥያቄ - ማለትም (ሕዝብን የሥልጣን ምንጭና የሥልጣን ባለቤት የመሆንና የማድረግ ...
- የሕግ የበላይነት ጥያቄ - ማለትም ማንም ሰው (መንግሥት ነኝ የሚል አካልም ጭምር) ከሀገሪቱ ሕግ  በላይ ሊሆን አይገባውም። ማንም ሰው ያለ ሕግ በተለይም በአመለካከቱ፣ በአስተሳሰቡ ሊታሠር፣ ሊገደል፣ ሊሰደድ፣ ሊጋዝ፣ ሊሰቃይ፣ የተለዬ አመለካከት

ወይም አስተሳሰብ ስላለውና ስለገፋ፣ የሀገሪቱን ሕግ (ሕገ-መንግሥት) አላግባብ ተገን አድርጎ ዜጋን ማስጨነቅና ማሳደድ ወዘተ. . . እንዳይኖር፤ በነገራችን ላይ በፖለቲካ ሳይሆን በወንጀል የሚፈለግም ሰው ቢሆን፣ የሃገሪቱ ሕግ በሚፈቅደው መንገድ እንዲስተናገድ የሚጠይቅ ወዘተ...

- ዜጎች በአገራቸው በኢትዮጵያ እንደዜጋ እኩል የሚኖሩበት፣ ሐገሪቱ በከርሰ ምድሯ የያዘችውን እምቅ ኃብት ሁሉም ዜጋ የሚጠቀምበትና የባለቤትነት ስሜት እንዲኖራቸው የማስቻል፤ የሐገሪቱን ሃብት ሁሉም ዜጋ በኩልነት የሚንከባከበው፣ የሚጠብቀውና ሊጠቀምበት የሚያስችለው እንዲሆን የሚጠይቅ ወዘተ . . . ዜጎች በአገራቸው ጉዳይ ላይ እኩል መብትና ድምጽ እንዲኖራቸው የሚያደርግ ወዘተ. . .
- የትምህርት እድል ለሁሉም ዜጋ በእኩል እንዲዳረስ
- የጤና አገልግሎት( ሕክምና) ሁሉም ዜጋ በአቅሙ እንዲያገኝ ወዘተ...
- ዜጋው በቋንቋውና በባህሉ ሳያፍር በዕኩልነት ተከብሮና ተጠብቆለት ሊጠቀም የሚችልበት ሁኔታ መኖር እንዳለበት የሚጠይቅ፤... ወዘተ

የጥያቄዎቹ አንኳር መልዕክቶች እነኝህ ናቸው።

EthioLion.com

ስለዚህ አቶ ሌንጮ! እነኝህ ከላይ የተዘረዘሩ መሠረታዊ ጥያቄዎች በውስጣቸውም መለስተኛ የሆኑ ጥያቄዎችን አቅፈው ይዘዋል። ለምሳሌ ከእነኝህ ሰፊ ይዘት ካላቸው ጥያቄዎች ውስጥ አንዱ የዴሞክራሲ መብት ጥያቄ ውስጥ የመደራጀት ጥያቄን ብንወስድ፣ ሴቶች በሴትነታቸው፣ ሠራተኞች በሠራተኝነታቸው፣ ተማሪዎች በተማሪነታቸው፣ አስተማሪዎች በአስተማሪነታቸው፣ ወጣቶች በወጣትነታቸው ጋዜጠኞች በጋዜጠኝነታቸው፣ ደራሲዎች በደራሲነታቸው ሊደራጁ የሚያስቸላቸው መብት ይፈቀድላቸው ይኖራቸው ለማለት ነው፤ በቀላል አማርኛ እነኝህ ጥያቄዎች የሰው ልጅ የማይገሠሥ መብቱ ሊሆን ይገባዋል ማለትም ጭምር ነው። ግንቦት 7/1997 ዓ.ም እነኝህን መጀመሪያ ከላይ የጠቀስኳቸውን መሠረታዊና ሊገሠሱ የማይገባቸው ጉዳዮች አንግቦ የተነሳ ትግል ነበር። ከግንቦት 1997 ምርጫ በፊትና እስከምርጫው ድረስ የተካሄዱ ትግሎች እነኝህን የሰው ልጅ ሊጠቀምባቸው የሚገቡ መሠረታዊ መብቶች በኢትዮጵያችን እንዲኖሩና እንዲመጡ፣ ከመጡም በኋላ እስከወዲያኛው እንዲከበሩም ለማድረግ፣ ያለማወላወል በቆራጥነት ከ193-200 በላይ የሰው ሕይወት ከፍሎ ህዝባችን የታገለበት ገድሉ ነው። ህዝባችን ለተዋደቀላቸው ለእነኝህ ክቡር መሠረታዊ መብቶችና

እሴት ማንም ሊደራደርበት መፍቀድ የለብንም ባይ ነኝ። የእነዚህ ጥያቄዎች ባለቤት ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ ነው። ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ማለት ሰፊው አርሶ አደር፣ ሠራተኛው (ላብ አደሩ፣) ወታደሩ፣ ተማሪው፣ አስተማሪው፣ ሴቶች፣ በተለይም የነገው ሃገር ተረካቢ ወጣቱ በጥቅሉ፣ በእነ አባዱላና ኦሕዴድ ሲረገጥ፣ ሲናቅ የነበረው ጭቁኑ ኦሮሞ፣ በእነ አዲሱ ለገሰው ኢሕዴን ሲረገጥ፣ የነበረው ጭቁኑ አማራ፣ ምርጫ እንዳይሳተፍና በተዘጋ ግርግም ውስጥ እንዲመርጥ የተደረገው የትግራይ ሕዝብ፣ በመብቱ እንዳይጠቀም ወይም በነጻ እንዲመረጥ ያልተፈቀደለት የጋምቤላ ሕዝብ፣ ሁሌም ምክነያት እየተፈጠረለት በነጻ ከተቀረው የሃገሪቷ ክፍል ጋር ለወጉ እንኳን ምርጫ እንዳያደርግ የሚታገደው የሶማሌ አካባቢ ህዝብ፣ በደቡብ የሚኖረው ህዝባችን በመምረጡ ብቻ በአግአዚ ጦር የተገደለው፣ ከቤቱ እንዲፈናቀለ የተደረገው፣ ቤት ንብረቱ የተዘረፈው፣ ወዘተ. . . በአጠቃላይ መብቱን ተጠቅሞ የመረጠውን የኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ በረሃብ፣ በኑሮ ውድነት፣ በችጋር የሚያሰቃዬው ወዘተ... ህዝብ ሁሉ የጋራ ጥያቄዎች ናቸው። ስለዚህም አቶ ሌንጮ ሆኑ ማንም በእነኝህ የሕዝብ ጥያቄዎችና ገድሎች ላይ መደራደር አይችልም። በእነኝህ መሠረታዊ ጥያቄዎች ላይ የሚያምን ኢትዮጵያዊ ሁሉ ደግሞ ሊጠብቃቸውና ለድርድር እንዳይገቡ ሊታገልላቸው ይገባዋል።

ሌላው ግንቦት 1997 ዓ.ም ህዝባችን ያስተማረንና የነገረን በእነኝህ መሰረታዊ ጥያቄዎች ዙሪያ 14 ዓመት ሙሉ በጉልበትና በመግደል ፀጥ አድርጎ ለመግዛት የሞከረውን የጠባብ ብሔርተኛ ገዥ ቡድን፣ በዓለም ፊት ያዋረደበት ነው። ምን ማለት ነው? በእነኝህ መሰረታዊና ሰፊ ይዘት ባላቸው የዴሞክራሲ ጥያቄዎች ዙሪያ የተፋጠጡት ጠባቡ ብሄርተኛው የወያኔ ገዥ ቡድን በአንድ በኩልና፣ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ በሌላ በኩል ቆመው ነው ማለት ነው። በዚህ ትግል ውስጥ ሰፊው የኦሮሞ ሕዝብ ከሌላው ወገኑ ጋር ሆኖ የአባ ዱላ ኦህዴድና የጠባብ ብሄርተኛው የወያኔ አገዛዝ በኢትዮጵያ ላይ ተመልሰው እንዳይመጣ በድምጹና በሞቱ ሕይወት ከፍሎ አስተምሮናል። አቶ ሌንጮ ወያኔ ይሄንን የጠባብ ብሄርተኝነት በሽታውን በትግራይ ውስጥ እንደኤይድስ እንደረጨው ሁሉ በኢትዮጵያ ህዝብ ውስጥ ለመርጨት ሲሞክር እርስዎም እንደሚያስታውሱት ገና ከትግራይ መሬት እንደነቀለ፣ የኢትዮጵያ ህዝብ እዚያው ትግራይ ውስጥ እንዲቀብረው አድርጎታል። ምስጋና ይገባዋል የኢትዮጵያ ሕዝብ። ዛሬ ዛሬ በዚህ የጠባብነት ዛር የሚያብዱ የሚያቅራሩ ካሉ፣ በባዶ በርሚል ውስጥ የሚጮሁ የገደል ማሚቶዎች ናቸው እላቸዋለሁ። ጠባብነት በ1983 ዓ.ም በሰፊው ኢትዮጵያ ሕዝብ ተገደለ፤ በ1997 ዓ.ም ደግሞ በኢትዮጵያዊነት ተገንዞ ላንዴና ለሁሌም ተቀበረ። ስለዚህ አቶ ሌንጮ ለታን

EthioLion.Com

የምነግራቸው አዎ! ከፕሮፌሰር ኤፍሬም ጋር ሰሞኑን መገናኘትዎን አልሸሸጉምና ይህንን በሕዝብ ትግል ሥልጣኑን እንዲለቅ የተጠየቀውን ጠባብና ዘረኛ የወያኔ አገዛዝ ጠጋግኖ ለማቆም መሯሯጥና መደገፍ፣ ከኦሮሞ ሕዝብ ትግል ጋር በፍጹም በፍፁም በዓይነቱና በይዘቱ የማይገናኝና "ዱባና ቅል አበቃቀላቸው ለየቅል" እንደሚባለው ነው እልዎታለሁ።

የኦሮሞ ሕዝብ ወትሮም ቢሆን ከእናንተ በፊት ከቀሪው ኢትዮጵያዊ ወገኑ ጋር ሆኖ ለመብቱ ታግሏል፤ ሲታገልም ኖሯል። አሁንም ይህንን በድምጹ የጣለውን ጠባብ የወያኔ ገዥ ቡድን እየታገለ ነው። ድምጹን ለማስመለስ ከሌላው ወገኑ ጋር ሆኖም እየተሟሟተ ይገኛል። ይህ የተጀመረ ትግል ጫፍ መድረሱ አይቀርምና እኔም ሆንኩ አቶ ሌነጮ በሕዝባችን ያልተቋረጠ ትግል ነጻ እንሆናለን ማለት ነው። አቶ ሌንጮ ሆይ! በእኔ ይሁንብዎ በግንቦት 1997 ዓ.ም የተሠራችው ኢትዮጵያ በገዥዎች የተድቦለቦለች ሳትሆን፣ በሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግልና ተጋድሎ በዴሞክራሲያዊ ድምጽ የቆመችና ማህተሙን ያስቀመጠባት ናት። ዛሬም በዚህ ህዝባዊና ዴሞክራሲያ የሕዝብ ድምጽና ተጋድሎ በተሠራችውና በተገነባችው ኢትዮጵያ ላይ ካልተስማማን፣ እንግዲህ መቸስ ማል ጎደኒ በማለት

እኛ እንደተማርነው በታሪክ ሲጣራ፣
ጅቡቲም የእኛ ናት እንኳንስ ኤርትራ።

በማለት እለየዎታለሁ። ኦ! ማእሌሽ ወዲ አፈወርቂ!

የሕዝብ ድምጽ ይከበር! የታሠሩ የፖለቲካ እስረኞች በሙሉ ይፈቱ!
ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!

ቸር ይግጠመን
ኦክቶበር 22/ 2008

EthioLion.com